*AMHARIC*

## ስለ መኒንጆካል Meningococcal በሽታ መረጃ
## ከ 6- 12 ክፍል

የተከበራችሁ ወላጆች/ ሞግዚቶች:

ይህን ደብዳቤ የላክንላችሁ ዋና ምክንያት በስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች የሚማር ተማሪ ስላልዎት ነው። በአንቀጽ RCW 28A.210.080, መሰረት ስለ ሜኒንጃይትስ እብጠት በሽታዎች አመጣጥና እንዴት መከላከል እንደሚቻል መረጃዎች ለህበረተሰቡ ማወቅ እንዳለብት ህጉ ያስገድዳል።ይህ በሽታ እስከ ሞት የሚያደርስ በጣም አደገኛ በሽታ ስለ ሆነ አስፈላጊውን መረጃ እንድታውቁት ይገባል።.

ሜኒንጃይትስ በሽታ የሚነሳው በጎሮሮና በአፍንጫ ውስጥ በሚኖሩ ከተለያዩ የባክተሪያ አይነቶች ነው የሚፈጠረው።ብዙ ጊዜ ለአቅመ አዳም የደረሱ ጎልማሳዎች በቀላሉ በሽታው ሊበከሉ ይችላሉ።የዚህ በሽታ ዋና ዋና ምልክቶች የሰውነት ሙቀት መጨመር፤ብርድ ወይም ጎንፋን፤ መንቀጥቀጥ፤ ሃይለኛ የራስ ምታት፤ ሰውነት ላይ ሽፍታ፤ አንገት ላይ እበጥ የመሳሰሉት ናቸው።በሽታው የሚተላለፈው በቀጥታ በሽታ ከያዘ ሰው ጋር በመሳሳም ሊተላለፍ ይችላል ወይም በሽታው የያዘው ሰው ሲያስነጥስ ወይም ሲያስለው፤ ወይም በሽታው የያዘው ሰው በነካከው እቃ ምግብ መብላት ወይም ውሃ መጠጣት በቀላሉ በሽታው ሊተላለፍ ይችላል።

የዋሽንግተን ስቴት የጤና ጥበቃ ክፍል ስለዚሁ በሽታ ሙሉ መረጃ እንዲኖራችሁና አስፈላጊው ጥንቃቄ እንድታደርጉና ከበሽታው ለመከላከል አስፈላጊ የሆነ ክትባት እንድትወስዱ ይጠይቃል። ክትባት በመውሰድ 83 ከመቶ በሽታው ለመካላከል ትችላላችሁ።ብዙ ጊዜ ክትባት እንዲከተቡ የሚደረገው ከ11 እስከ 12 እድሜ ክልል ላሉትና 15 አመት እድሜ ላላቸው ህጻናት ቢሆንም ሌሎች ወጣቶች ክትባት ቢወስዱም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ብለን እናምናለን። ትምህርት ቤት ለመማር ክትባት መወሰድ ግዴታ አይደለም።

የጤና ጥበቃ ክፍል ስለዚሁ በሽታ ሙሉ መረጃ እንድታገኙና ከየልጆቻችሁ ጤና ሃላፊዎች ጋር ስላለ ክትባት እንድትናጋገሩ አጥብቆ ይጠቃል። ስለዚህ በሽታ ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት የሚከተሉትን የኢንተርኔት አድራሻ ጎብኙ።

- **Public Health Seattle/King County --** (206) 296-4600
  www.metrokc.gov/health/immunization/clinics.htm

- **Washington State Department of Health Immunization Program**
  www.doh.wa.gov/cfh/Immunize/meningococcal.htm

- **Centers for Disease Control and Prevention**
  Vaccine Information: www.cdc.gov/nip/publications/vis/vis-mening.pdf
  Disease Information: www.cdc.gov.ncidod/dbmd/diseaseinfo/meningococcal_g.htm
  Fact Sheets: www.cdc.gov/nip/vaccine/meninig/mening_fs.pdf

ፕሮግራም ማናጀር
የተማሪዎች ጤና አገልግሎት ክፍል
ስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች

Adopted September 2005